የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፸፰
አዲስ አበባ ነሐሴ ፩ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

23rd Year No.78
ADDIS ABABA, 7th August, 2017

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፶/፪ሺ፱ ዓ.ም
የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ማቋቋሚያ (ማሻሻያ) አዋጅ ………………………………………………ገጽ ፱ሺ፰፻፳፬

## CONTENT

PROCLAMATION No. 1050/2017
Ethiopia Commodity Exchange Establishment (Amendment) Proclamation ……………………………………page 9824

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፶/፪ሺ፱

**<u>የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ</u>**

የኢትዮጵያ ምርት ገበያ የተቋቋመበትን ዓላማ ለማሳካት የምርት ገበያውን ተደራሽነት የበለጠ በማስፋት የግብይት ተዋናዮችን ፍላጎትና አነስተኛ አምርቾች በገበያው ያላተቸውን ተሳትፎ ማሳደግ የሚያስችል አሰራር መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፣

የግብርና ምርቶች በዓይነት በመጠንም ሆነ በጥራት ወጪ ቆጣቢ በሆነ ሁኔታ ወደ ምርት ገበያው የሚቀርቡበትን አመቺ ሁኔታ በመፍጠር በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ በማድረግ የአገሪቱን የውጭ ንግድ በማጠናከር የምርት ገበያውን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፭፻፶/፲፱፻፺፱ን እንደገና ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭ (፩) መሰረት እንደሚከተለው ታውጇል;-

Proclamation No. 1050/2017

**<u>A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE AMENDMENT OF THE ETHIOPIA COMMODITY EXCHANGE ESTABLISHMENT PROCLAMATION</u>**

**WHER AS,** it is found necessary to satisfy the customer demand and increase the small scale farmers participation in the exchange by develop procedures and by enhance the accessibility of Ethiopia commodity exchange to achieve their objectives ;

**WHERE AS**, it is found necessary to re-amend the Ethiopia Commodity Exchange Establishment proclamation no.550/2007 in a way it receives the agricultural product in their type ,quality , amount and in a cost effective manner and make them competitive to foreign market there by enhance the country foreign trade;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with sub-article (1) of Article 55 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:



www.chilot.me

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ማቋቋሚያ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፶/፪ሺ፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. <u>ማሻሻያ</u>**

የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፭፻፶/፲፱፻፺፱ (እንደተሻሻለው) እንደሚከተለው እንደገና ተሻሽሏል;-

፩/ የአዋጁ አንቀጽ ፪ (፮) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፮) ተተክቷል፦

"፮/ 'ውል' ማለት ለምርት ገበያ ግብይት ሲባል አንድን ምርት ለመግዛት ወይም ለመሸጥ ወጥ ሆኖ የተዘጋጀና የምርቱን መጠን፣ ዋጋ፣ ደረጃ፣ መነሻ ቦታ፣ ተፈጻሚ የሚሆንበትንና የምርቱ ርክክብ የሚፈጸምበትን ቀን በዝርዝር የሚያካትት ስምምነት ነው፤"

፪/ የአዋጁ አንቀጽ ፪ (፲፫) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፲፫) ተተክቷል፦

"፲፫/ 'ሚኒስቴር' ማለት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የንግድ ሚኒስቴር ነው፤"

፫/ ከአዋጁ አንቀጽ ፪ (፲፭) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፲፮) ተጨምሯል፦

"፲፮/ 'ጥብቅ የማቆያ ሥፍራ' ማለት በምርት ገበያው ግብይት የሚካሄድበትን ምርት የያዙ የጭነት ተሽከርካሪዎች ጭነቱ ተሽከርካሪው ላይ እንዳለ ተሸጦ ወደገዥ እስከሚተላለፍበት ወይም በምርት ማከማቻ መጋዘን እስከሚራገፍበት ድረስ ባለው ጊዜ የሚቆሙበት የተከለለና ደህንነቱ የተጠበቀ ቦታ ነው፡፡"

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "Ethiopia Commodity Exchange Establishment (Amendment) Proclamation No. 1050 /2017".

**2. <u>Amendment</u>**

The Ethiopia Commodity Exchange Establishment Proclamation No.550/2007 (as amended) is here by re-amended as follows:

1/ Sub-article (6) of Article 2 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new sub-article (6):

"6/ 'contract' means a standardized agreement prepared to buy or sell a specified commodity containing details such as amount, grade, price and origin of the commodity and the date on which the contact will mature and become deliverable for purposes of trading on the Exchange;"

2/ Sub-article (13) of Article 2 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new sub-article (13):

"13/ 'Ministry' means the Ministry of Trade of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;"

3/ The following new sub-article (16) is added after sub-article (15) of Article 2 of the Proclamation:

"16/ 'bonded yard' means fenced secured yard constructed for parking trucks loaded with commodity to be traded in the Exchange until the consignment is sold on truck and picked up by the buyer within the maximum pick up period or deposited to warehouse;"

www.chilot.me

፬/ የአዋጁ አንቀጽ ፬ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፬ ተተክቷል፡-

“፬. **ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን**

የንግድ ሚኒስቴር የምርት ገበያው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል፡፡”

፭/ ከአዋጁ አንቀጽ ፮ (፲) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፲፩) እና (፲፪) ተጨምረዋል፡-

“፲፩/ ስትራተጂያዊ በሆኑ የአገሪቱ አካባቢዎች ዘመናዊና በቴክኖሎጂ የተደገፉ የምርት ማከማቻ መጋዘኖችን እና ጥብቅ የማቆያ ሥፍራዎችን መገንባትና ማስተዳደር፤

፲፪/ በምርት ገበያው ግብይት የሚደረግባቸው ምርቶች የሚጓጓዙበትን ሁኔታ በተመለከተ እንደአስፈላጊነቱ አግባብነት ካለው የመንግሥት አካል በሚሰጠው ውክልና መሠረት አስገዳጅ መስፈርት ማውጣት፤ ተፈጻሚነቱን የማረጋገጥ እና ተገቢውን እርምጃ የመውሰድ፡፡”

፮/ የአዋጁ አንቀጽ ፯ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፯ ተተክቷል፡-

“፯. **ካፒታል**

የምርት ገበያው የተፈቀደ ካፒታል ፩ ቢሊዮን ፪፻፶ ሚሊዮን (አንድ ቢሊዮን ሁለት መቶ ሃምሣ ሚሊዮን) ብር ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፯፻፳፭ ሚሊዮን (ሰባት መቶ ሃያ አምስት ሚሊዮን ብር) በዓይነትና በጥሬ ገንዘብ ተከፍሏል፡፡”

፯/ ከአዋጁ አንቀጽ ፰ (፮) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፯) ተጨምሯል፡-

"፯/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳ (፩) የተደነገገው ቢኖርም በምርት ገበያው የአባልነት መቀመጫ

4/ Article 4 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Article 4:

“4. **Supervising Authority**

The Ministry of Trade shall be the supervising authority of the Exchange.”

5/ The following new sub-articles (11) and (12) are added after sub-article (10) of Article 6 the Proclamation:

“11/ to construct and manage modern and technology based commodity warehouses and bonded yards in strategic locations of the country;

12/ define mandatory criteria for condition of transport of exchange traded commodities and follow up its implementation, as may be delegated by appropriate government authority.”

6/ Article 7 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Article 7:

“7. **Capital**

The authorized capital of the Exchange is Birr 1,250,000,000 (One Billion, Two Hundred Fifty Million) of which Birr 725, 000,000 (Seven Hundred Twenty-Five Million) is paid in cash and in kind.”

7/ The following new sub-article (7) is added after sub-article (6) of Article 8 of the Proclamation:

“7/ Notwithstanding sub-article (2) of this Article and sub-article (1) of Article 20 of the Proclamation, detail conditions under

www.chilot.me

ሳይኖራቸው ያለአገናኝ በምርት ገበያው በራሳቸው መገበያየት የሚችሉ ምርት ሻጮች ወይም ገዥዎች የሚስተናገዱበት ዝርዝር ሁኔታ በምርት ገበያው የውስጥ ደንብ ይወሰናል፡፡"

፰/ የአዋጁ አንቀጽ ፲፩ (፩) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተተክቷል፦

"፩/ የዳይሬክተሮች ቦርድ አስራ አንድ አባላት የሚኖሩት ሲሆን ሰብሳቢውን ጨምሮ ስድስቱ በሚኒስቴሩ ይሰየማሉ፤ አምስቱ በምርት ገበያው የውስጥ ደንብ መሰረት ከአባላት ወይም ከአባል ማህበራት ይመረጣሉ፡፡"

፱/ ከአዋጁ አንቀጽ ፲፭ (፱) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፲) ተጨምሯል፦

"፲/ የምርት ገበያውን አደረጃጀትና መዋቅር ያጸድቃል፡፡"

፲/ የአዋጁ አንቀጽ ፳ (፪) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተተክቷል፦

"፪/ ስለምርቱ ጥራት ወይም ደረጃ ከምርት ገበያው የምርት የምስክር ወረቀት ሳያገኝ እንዲሁም ስለምርቱ መጠን፣ መነሻ ቦታ ሁኔታና የማከማቻ መጋዘኑ ወይም ጥብቅ ማቆያው የሚገኝበትን ቦታ የሚገልጽ የመጋዘን ማከማቻ ደረሰኝ ሳይኖረው ምርቱን በምርት ገበያው ለግብይት ማቅረብ የተከለከለ ነው፡፡"

፲፩/ የአዋጁ አንቀጽ ፳፪ (፩) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተተክቷል፦

"፩/ የምርት ገበያው ከግብርና ምርቶች ጋር በተያያዘ ወዲያውኑ የሚፈጸም ወይም ርክብክባቸው ወደፊት የሚፈጸም ወይም ወደፊት በሚፈጸሙ ውሎች ላይ ተመስርቶ ይሰራል፡፡"

which non-members of the Exchange may buy or sell their own commodities at the Exchange plat without intermediary shall be determined in the rules of the Exchange."

8/ Sub-article (1) of Article 11 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new sub-article (1):

"1/ The Board of Directors shall consist of eleven members, of whom six, including the chairperson, are assigned by the Ministry and five are elected from Members or Members' Associations in accordance with the rules of the Exchange."

9/ The following new sub-article (10) is added after sub-article (9) of Article 15 of the Proclamation:

"10/ Approve the organizational structure of the Exchange."

10/ Sub-article (2) Article 20 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new sub-article (2):

"2/ It shall be prohibited to trade a commodity on the Exchange without the issuance of an Exchange product certificate as to the product quality or grade and of an Exchange warehouse receipt as to the product origin, quantity, condition, and location of warehouse or bonded yard."

11/ Sub-article (1) of Article 22 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new sub-article (1):

"1/ The Exchange shall operate with spot or future contracts or forward contracts in agricultural commodities."

12/ The following new sub-articles (3) and (4) are

www.chilot.me

፲፪/ ከአዋጁ አንቀጽ ፳፪ (፪) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፬) ተጨምረዋል፡-

“፫/ በምርት ገበያው ግብይት የሚደረግባቸው ርክክባቸው ወደፊት የሚፈጸም እና ወደ ፊት የሚፈጸሙ ውሎችን በተመለከተ ዝርዝሩ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያና በምርት ገበያው የውስጥ ደንብ ይወሰናል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም በሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ባለው የመንግሥት አካል መጽደቁ እንደተጠበቀ ሆኖ የምርት ገበያው ከግብርና ምርቶች ውጭ ያሉ ውሎችን በማጥናት ሊያገበያይ ይችላል፡፡”

፲፫/ የአዋጁ አንቀጽ ፳፫ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተተክቷል፡-

“፫/ የኢትዮጵያ ደረጃዎችን አጽድቆ ለማውጣት በህግ ሥልጣን የተሰጠው አካል እንደተጠበቀ ሆኖ ምርት ገበያው በዚህ አንቀጽ የተሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፡፡”

፲፬/ ከአዋጁ አንቀጽ ፳፱ ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፴ ተጨምሮ ነባሮቹ አንቀጾች ከ፴ እስከ ፴፫ የሚገኙት እንደቅደም ተከተላቸው አንቀጽ ፴፩፣ ፴፪፣ ፴፫ እና ፴፬ ሆነው ተሸጋሽገዋል፡-

**“፴. <u>ባለቤትነትን እና የምርት ዱካን ባስጠበቀ ሁኔታ ስለሚደረግ ግብይት</u>**

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፪ (፬) ስለምርት ተተካኪነት የተደነገገው ቢኖርም የምርት ገበያው የምርቱን ባለቤት ማንነት እና የምርቱን ዱካ ያረጋገጠ የግብይት ሥርዓት ሊዘረጋ ይችላል፡፡

added after sub-article (2) of Article 22 of the Proclamation:

“3/ The conditions under which future contracts or forward contracts in agricultural commodities traded at the exchange shall be provided in the directive to be issued by the Authority and the rules of the exchange.

4/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, the Exchange may, after conducting a study, trade in other contracts outside contracts in agricultural commodities subject to the prior approval of the Ministry or other pertinent government authority.”

13/ Sub-article (3) of Article 23 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new sub-article (3):

“3/ Without prejudice to the Ethiopian Standards Agency approved to given authorized body the Exchange shall carry out its duties under this Article.”

14/ The following new Article 30 is added after Article 29 of the Proclamation and the existing Articles 30 to 33 are respectively renumbered as Article,31, 32,33 and 34:

**“30. <u>Identity preserved and Traceable Commodities</u>**

1/ Notwithstanding sub-article (4) of Article 2 of this Proclamation regarding interchangeability of commodities, the Exchange may establish a trading system that ensures the identity of the owner or supplier and traceability of commodities.

www.chilot.me

፪/ ባለቤትነትን እና የምርት ዱካን ባስጠበቀ ሁኔታ በሚደረግ ግብይት መካተት ያለባቸው ምርቶች ዝርዝር ሚኒስቴሩ በየጊዜው እየከለሰ ሊወስን ይችላል፡፡

፫/ በዚህ ሥርዓት ግብይት የሚፈጸምባቸው ምርቶች የመጋዘን ውስጥ የምርት አቀማመጥ፣ አስተዳደርና ርክክብም የምርቱንና የባለቤቱን ወይም አቅራቢውን ማንነት የሚያረጋግጡ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

፬/ በዚህ ሥርዓት ግብይት የሚደረግበትን ምርት እንደጫኑ በምርት ገበያው ጥብቅ ማቆያ ሥፍራ ግብይት የሚካሔድባቸውን ተሽከርካሪዎችና ጭነቶች አቀባበል፣ ናሙና አወሳሰድ፣ ደረጃ አወሳሰን፣ የክብደት ምዘና፣ ግብይት፣ ርክክብና የአደጋ ቁጥጥር አሠራሮችን የተመለከቱ ዝርዝር የአሠራር ሥርዓት በምርት ገበያው ደንብ ይወሰናል፡፡”

## ፫. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከሰኔ ፳፬ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ ፩ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም**

**ሙላቱ ተሾመ (ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚደንት**

2/ The kind of commodity to be included to trade in the Exchange by maintaining identity of owner or preserving identity may be decided by the Ministry by revising from time to time.

3/ Staking, inventory and delivery of commodities at the Exchange`s warehouse through such trading system shall also be done by ensuring identity of the commodity and that of its owner/supplier.

4/ Detail rules governing on truck trading of identity preserved commodities at the Exchange`s Bonded Yard, handling of arrivals, sampling, grading, weighing, trading, and risk management shall be determined in the Rules of the Exchange.”

## 3. Effective Date

This Proclamation shall enter in to force as of July 1, 2017.

**Done at Addis Ababa this 7th day August of 1017.**

**MULATU TESHOME (DR)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

www.chilot.me